
# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ



# የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅቶች
# የአሰራር መመሪያ ቁጥር 21/2013

# 1. መግቢያ

በከተማችን አዲስ አበባ ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ውስጥ 76 ፐርሰንት የሚሆነው በህብረት የሽርክና ጽዳት ማህበራት ከመኖሪያ ቤት የሚሰበሰብ ደረቅ ቆሻሻ ሲሆን ይህ ደረቅ ቆሻሻ ክፍለ ከተማው በሚሰጠው የመንግስት ተሽከርካሪ ስምሪት አማካኝነት ከጊዚያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማቆያ ቦታዎች እየተሰበሰበ ወደ ማስወገጃ ቦታ እንዲጓጓዝና እንዲወገድ እየተደረገ ይገኛል፡፡

ነገር ግን በከተማው የሚመነጨው የደረቅ ቆሻሻ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ይህንን ደረቅ ቆሻሻ በመንግስት ተሽከርካሪ ብቻ ማጓጓዝ አዳጋች አድርጎታል፡፡ ስለዚህ ኤጀንሲው በከተማው በተለያዩ ምክንያት በህብረት የሽርክና የጽዳት ማህበራት፤ በመንገድ የጽዳት ሰራተኞች፤ በህብረተሰቡ የጽዳት ተሳትፎ፤ በምግብ ዋስትና በተደራጁ ሰዎች የፀዳና የተሰበሰበን ደረቅ ቆሻሻ እንዲሁም በህገወጥ መንገድ በየቦታው ተጥለው የተከማቹ ደረቅ ቆሻሻዎችን በተቀመጠው የማጓጓዝ ስታንዳርድ መሰረት ተጓጉዞ እንዲወገድ ለማድረግ እንዲሁም በዘርፉ የሚታዩ የደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዝ ስርዓትን በተገቢው ሁኔታ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ለማሻሻልና አሁን ያለውን ችግር ለመፍታት ያስችል ዘንድ በመንግስት ተሽከርካሪ ሲጓጓዝ የነበረን ደረቅ ቆሻሻ በኮንትራት ደረቅ ቆሻሻ ለሚያጓጉዙ ድርጅቶች እንዲሰሩት የሚስችል የአሰራር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **"በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅቶች የአሰራር መመሪያ ቁጥር ፳፩/፪ሺ፲፫"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ዓላማ

ከከተማው በተለያየ መንገድ ተሰብስቦ በመንግስት ተሽከርካሪ ሲጓጓዝ የነበረን ደረቅ ቆሻሻ በኮንትራት በግል ድርጅቶችና በህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት እንዲጓጓዝ በማድረግ የከተማውን የደረቅ ቆሻሻ የማጓጓዝ አቅምን ማሳደግና የከተማውን ጽዳት ማሻሻል፡፡

### ፫. የቃላት ትርጓሜ

የቃላት አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጣቸው በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡

፪. **"ኤጀንሲ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፡፡

፫. **"ደረቅ ቆሻሻ"** ማለት የንብረቱ ባለቤት ጥቅም የማይሰጥ ወይም የማይፈለግ ብሎ የሚጥለው ጠጣር ወይም ከፊል ጠጣር የሆነ ቁስ ነው፡፡

፬. **"የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት"** ማለት በግል፣ በማህበር፣ በሽርክና፣ በዩኒዬን፣ ወዘተ ደረቅ ቆሻሻን በተሽከርካሪ ለማጓጓዝ የተመዘገበ ድርጅት ሆኖ በህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበራት ተሰብስቦ በጊዚያዊ ማቆያ ቦታ የተከማቸን ደረቅ ቆሻሻን ወደ ማቃጠያ ማዕከል፣ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከላት ወይም ማስወገጃ ቦታ የሚያጓጉዝ ድርጅት ማለት ነው፡፡

፭. **"የግል የጽዳት ድርጅት"** ማለት በግል፣ በማህበር፣ በሽርክና፣ በዩኒዬን ተደራጅተው ደረቅ ቆሻሻን ከመኖሪያ ቤት ውጪ ማለትም ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት፣ የንግድ ማዕከላት፣ ሆቴሎች ወዘተ ዞረው እየሰበሰቡ ወደ ማቃጠያ ማዕከል፣ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከላት ወይም ማስወገጃ ቦታ በተሽከርካሪ የሚያጓጉዙ ድርጅቶች ናቸው፡፡

፮. **"ምድብ"** ማለት ከረጲ ማስወገጃ ቦታ በአማካይ ተቀራራቢ ርቀት ያላቸው ክፍለ ከተሞች ለኮንትራት ስራ ክፍያ ያመች ዘንድ የሚለዩበት ድልድል ነው፡፡

## ፬. መመሪያውን ማውጣት ያስፈለገበት ምክንያት፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ በመንግስት ተሸከርካሪ የሚጓጓዘው የደረቅ ቆሻሻ መጠን ከፍተኛ ሲሆን ይህንን ደረቅ ቆሻሻ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት በመንግስት ተሸከርካሪ በስታንዳርዱ መሰረት ማጓጓዝና ማስወገድ ባለመቻሉ በከተማው ጽዳትና በአካባቢ ብክለት ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ ይገኛል፡፡ በተለይ በህብረተሰቡ ዘንድ ቆሻሻው በወቅቱ ስለማይነሳና አካባቢን ስለሚበክል በከተማችን አንዱ የቅሬታ ምንጭ እየሆነ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የህብረት የሽርክና ጽዳት ማህበራት የሰበሰቡት ደረቅ ቆሻሻ በፍጥነትና በወቅቱ ስለማይነሳላቸው በዚህም ምክንያት የገቢ መጠናቸው ስለሚቀንስ በመንግስት ላይ ከፍተኛ እንዲያነሱ እያደረጋቸው ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ በከተማው ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዝ ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ ማከናዎን ባለመቻሉ የከተማውን ጽዳት በሚፈለገው ደረጃና ህብረተሰቡ በሚጠይቀው ልክ ማሻሻል አልተቻለም፡፡ ስለዚህ ይህ መመሪያ ከላይ የተዘረዘሩ ችግሮችን በመፍታት የምልልስ መጠንን በማሻሻል በከተማው የሚከማችን የደረቅ ቆሻሻ መጠን  በመቀነስ  የከተማውን ጽዳት ለማሻሻልና የህብረተሰቡን ቅሬታ ለመፍታት አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡

## ፭. የመመሪያው ወሰን

የዚህ መመሪያ ወሰን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚገኙ የህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበራት ከቤት ለቤት፤ ከመንገድ ጽዳት፤ በህብረተሰቡ ከዞን ጽዳት፤ በምግብ ዋስትና በተደራጁ ነዋሪዎች የተሰበሰበን እንዲሁም ከህገወጥ ቆሻሻ መጣያ ቦታ ወዘተ ተሰብስቦ በጊዚያዊ ማከማቻ ቦታ በህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት አማካኝነት የተከማቸን ደረቅ ቆሻሻ በተሸከርካሪ ጭነው ወደ ማስወገጃ ቦታ፤ ማቃጠያ ማዕከል ወይንም የመልሶ መጠቀም ማዕከላት የማጓጓዝ አገልግሎት በሚሰጡ ድርጅቶ ላይ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ፮. ደረቅ ቆሻሻ የሚጓጓዝባቸው ክፍለ ከተሞች ምድብ

፩. ክፍለ ከተሞች ከረጺ ማስወገጃ ቦታ ያላቸውን ርቀት መሰረት በማድረግ በሁለት ምድብ ማለትም ምድብ አንድና፣ ምድብ ሁለት በማለት ተከፍሏል፡፡

**ምድብ አንድ**

1. ንፋስ ስልክ
2. ኮልፌ
3. ልደታ
4. ቂርቆስ
5. አዲስ ከተማ
6. አራዳ

**ምድብ ሁለት**

1. ቦሌ
2. የካ
3. አቃቂ ቃሊቲ
4. ጉለሌ

፪. ክፍለ ከተሞች በሁለት ምድብ የተመደቡበት ሂደት ከረጺ ማስወገጃ ቦታ ያላቸውን ርቀት ግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን በዚህም መሰረት ምድብ አንድ የሚባሉት ክፍለ ከተሞች ለማስወገጃ ቦታው በአማካይ 12.8 ኪሎ ሜትር የሚርቁ ሲሆን፣ ምድብ ሁለት የሚባሉት ደግሞ ከማስወገጃ ቦታው በአማካይ 24.9 ኪሎ ሜትር የሚርቁ ናቸው፡፡

፫. በምድብ አንድና በምድብ ሁለት የተመደቡ ክፍለ ከተሞች ከማስወገጃ ቦታ የተለያየ ርቀት ያላቸው በመሆኑ የተሽከርካሪ ምልልስ መጠናቸው፣ የነዳጅ፣ የቅባት፣ የዘይት ወዘተ ወጭ የተለያየ በመሆኑ ቆሻሻውን ለማጓጓዝ የሚከፈላቸው ክፍያም እንደምድባቸው ሁለት ዓይነት ዋጋ ይሆናል ፡፡

፬. በተራ ቁጥር ፫ በተገለፀው መሰረት በምድብ አንድ ለተመደቡ ክፍለ ከተሞች ለሚያጓጉዙት ደረቅ ቆሻሻ የክፍያ መጠኑ ለአንድ ሜትር ኩብ ብር 24 ወይንም አንድ ኪሎ ግራም 0.12 ሳንቲም ሲሆን ለምድብ ሁለት ደግሞ የክፍያ መጠኑ ለአንድ ሜትር ኩብ ብር 38 ወይንም ለአንድ ኪሎ ግራም 0.19 ሳንቲም ነው፡፡

## ፯. ደረቅ ቆሻሻ ለማጓጓዝ የኮንትራት ስራ ለመወዳደር አስፈላጊ መስፈርት

፩. ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት የኮንትራት ስራ ላይ ለመወዳደር የሚከተሉትን መስፈርቶችን ማሟላት ይገባዋል፡፡

1.1 ደረቅ ቆሻሻን ለማጓጓዝ የሚያስችል የስሪት ዘመኑ 20 ዓመት ያልበለጠው ቢያንስ ሁለት ባለ 40 ሜትር ኩብ እና በላይ መጫን የሚችል ኮምፓክተር ተሽከርካሪ በድርጅቱ ወይንም በግለሰቡ ስም ያለው፡፡ ነገር ግን ድርጅቱ አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ካለው ከሌላ ተመሳሳይ መስፈርት የሚያሟላና አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ካለው ድርጅት ጋር በጋራ በራሳቸው ተቀናጅተው መመዝገብ ይችላሉ፡፡

1.2 ከዚህ በፊት ከኤጀንሲው ጋር ውል ገብቶ ደረቅ ቆሻሻ ከተቋማት ሲሰበስብ የቆየ የግል የጽዳት ድርጅት ሆኖ ነገር ግን በዚህ በደረቅ ቆሻሻ አጓጓዝ ስራ ለመወዳደር ከፈለገ በቅድሚያ ከኤጀንሲው በዚህ ስራ እንዲወዳደር የድጋፍ ደብዳቤ ሊሰጠው ይገባል፡፡

1.3 ከዚህ በፊት ከኤጀንሲው ጋር ውል ገብቶ ደረቅ ቆሻሻ ሲሰበስብ የቆየ የግል የጽዳት ድርጅት ወይም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ከሆነ ከሚሰራበት ክፍለ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ ከማስወገጃ ቦታ ወይም ከደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ ማዕከል በአሰራር ላይ ችግር የሌለበት ለመሆኑ የድጋፍ ደብዳቤ ያለው መሆን ይገባዋል

1.4 በዘርፉ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያለው

1.5 ዓመታዊ የተሽከርካሪ ቴክኒካል ምርመራ ውጤትና የታደሰ የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ ያለው

1.6 በድርጅቱ ወይም በግለሰቡ የተመዘገቡት ኮምፓክተር ተሽከርካሪዎች (GPS) የተገጠመላቸው ሆኖ ጂፒኤሱ አገልግሎት የሚሰጥ ለመሆኑ በኤጀንሲው ባለሙያዎች ማስረጃ ማቅረብ፡፡ ነገር ግን ተሽከርካሪዎች ጂፒኤስ እንዲያሟሉ ሚገደዱት ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ይሆናል፡፡

1.7 በስራ ላይ የሚገኙ ሹፌርና ረዳት ሰራተኞች የጤንነት ምርመራና የቴታነስ ክትባት መረጃ ያላቸው

## ፰. የደረቅ ቆሻሻ የአጓጓዥ ድርጅት አመዘጋገብ

፩. ኤጀንሲው የደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዝ አገልግሎትን በኮንትራት ለማሰራት በጋዜጣ ማስታወቂያ በማውጣት እንዲሁ በኤጀንሲው የማስታወቂያ ቦርድ ላይ እንዲለጠፍ በማድረግ ተወዳዳሪዎች እንዲመዘገቡ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ ይህ ማስታወቂያ በክፍለ ከተማም እንዲለጠፍ በማድረግ አቅም ያላቸው የህብረት ሽርክና ማህበራት እንዲመዘገቡ ማድረግ ይገባል፡፡

፪. ደረቅ ቆሻሻን ለማጓጓዝ የሚመዘገብ ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅቶች በዚህ መመሪያ በአንቀጽ ፯ ከቁጥር 1.1 — 1.7 የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ህጋዊ የድርጅቱን ማህተም አድርጎ ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቦታ ቀርቦ የመመዝገብና ሰነዱን የማስገባት ግዴታ አለበት፡፡

፫. ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ደረቅ ቆሻሻን ከህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበራት ለማጓጓዝ ሲወዳደር ኤጀንሲው በእጣ በሚመድበው በየትኛውም ወረዳና የስራ ቦታ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

፬. የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅቶች ምዝገባ የሚከናዎነው ኤጀንሲው በየዓመቱ ግልጽ ማስታወቂያ በማውጣት ሁሉም ተወዳዳሪዎች በግልጽ እንዲመዘገቡ በማድረግ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ምንም ዓይነት ምዝገባም ይሁን ድልድል በኤጀንሲው ማከናዎን የተከለከለ ነው፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፬ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዝ ድርጅት እጥረት ካጋጠመው ወይንም በተለያዩ ምክንያቶች ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዘው ድርጅት ውሉ ከተቋረጠ ውሉ የተቋረጠበት ድርጅት ሲሰራበት የነበረው ቦታ ክፍተት እንዳይፈጥረ በማናጅምነት አስፈቅዶ ዓመት ሳይሞላው በውስጥ ማስታወቂያ በመለጠፍ ብቻ መስፈርቱን የሚያሟሉ ድርጅቶችን ምዝገባ አድርጎ ድልድል ሊያደርግ ይችላል ወይንም የተሻለ አፈጻጸም ያለውን ድርጅት በማናጅመንት አጸድቆ ለጊዜው መድቦ ሊያሰራ ይችላል፡፡

፯. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ተሸከርካሪ ገዝቶ የራሳቸውን ደረቅ ቆሻሻ ሲያጓጉዙ ያለውድድር የሚሰጣቸው ሲሆን ነገር ግን እንደማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት በፕሮግራሙ መሰረት ቀርበውና አስፈላጊውን ሰነድ አሟልተው የመመዝገብ ግዴታ አለባቸው፡፡

## ፱. የቴክኒካል ኮሚቴ አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት

፩. የቴክኒካል ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት ደረቅ ቆሻሻ ለማጓጓዝ የተመዘገቡ ድርጅቶች ያቀረቡትን ሰነድ በመመርመር መስፈርቱን የሚያሟሉና የማያሟሉትን ለይቶ ለኤጀንሲው ማናጅምነት በማቅረብ እንዲፀድቅ በማድረግ ቴክኒካል ምዘናውን ያለፉትን እጣ እንዲያወጡ ያደርጋል፡፡

፪. የቴክኒካል ኮሚቴው ለውድድር የቀረቡ ሰነዶችን የሚመዝነው በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፯ በቀረበው መስፈርት መሰረት ይሆናል፡፡

፫. የቴክኒካል ኮሚቴው አባላት እጩዎች የስም ዝርዝር በተቋሙ ስራ አስኪያጅ ቀርቦ ሲፀድቅ በደብዳቤ የሚወከሉ ይሆናል፡፡

፬. የቴክኒካል ኮሚቴው አባላት በየአመቱ በማናጅምንቱ ቀርበው ሲፀድቅ በደብዳቤ የሚወከሉ ሲሆን ነገር ግን ማናጅምንቱ ካመነበት እስከ ሶስት ጊዜ እንዲሰሩ ሊያደርግ ይችላል ነገር ግን ከሶስት ጊዜ በላይ እንዲሰሩ አይገደዱም፡፡

፭. የቴክኒካል ኮሚቴው አባላት፣ ብዛትና የስራ ድርሻ ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ መሰረት የሚከናዎን ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | የኮሚቴው አባላት | ብዛት | የስራ ድርሻ |
|---|---|---|---|
| 1 | የጠቅላላ አገልግሎትና ግዥ | 1 | አባል |
| 2 | የላንድፊል ዳይሬክቶሬት | 1 | አባል |
| 3 | የለውጥ ቡድን መሪ | 1 | አባል |
| 4 | የደረቅ ቆሻሻ ማስተባበሪያ አገልግሎቶች ዳይሬክቶሬት | 1 | ሰብሳቢ |
| 5 | ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት | 1 | አባል |
| | ድምር | 5 | |

## ፲. የቴክኒካል ምዘናና ውጤት አገላለጽ

፩. ደረቅ ቆሻሻን ለማጓጓዝ ከተመዘገቡ የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅቶች መካከል በኤጀንሲው የቴክኒክ ኮሚቴ ማጣራት ተደርጎ መስፈርቱን የሚያሟሉት ተለይተው በኤጀንሲው ማናጅመንት ሲፀድቅ በኤጀንሲው የማስታወቂያ ቦርድ ላይ የቴክኒክ ምዘናውን ያለፉ ድርጅቶችና የተሸከርካሪዎቻቸው ዝርዝር ይለጠፋል፡፡

፪. ደረቅ ቆሻሻን ለማጓጓዝ ከተመዘገቡ የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅቶች መካከል መስፈርቱን የማያሟሉና ያልተመረጡ ድርጅቶች ወይም ተሽከርካሪዎች ካሉ ቴክኒካል ኮሚቴው ለኤጀንሲው ማናጅመንት አቅርቦ በማፀደቅ በኤጀንሲው የማስታወቂያ ቦርድ ላይ ያልተመረጡበት ምክንያት ተገልፆ ዝርዝራቸው ይለጠፋል፡፡

፫. ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት በቴክኒካል ኮሚቴ ምዘና ድርጅቱ ወይም ተሽከርካሪው ካልተመረጠና ድርጅቱ ቅሬታ አለኝ ካለ የምዘና ውጤቱ በማስታወቂያ ከተለጠፈ 5 የስራ ቀናት ውስጥ በህጋዊ ደብዳቤ ቅሬታውን ለተቋሙ ስራ አስኪያጅ ማቅረብ ይችላል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፫ በተገለጸው መሰረት ቅሬታ ላቀረበ ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት የቅሬታ ማቅረቢያ ቀን ከተጠናቀቀ በኋላ ባሉት ሶስት ቀናት ውስጥ ሁሉም የቴክኒካል ኮሚቴው አባላት በተገኙበትና ቅሬታ አቅራቢው ድርጅት በተገኘበት ለቅሬታው ማብራሪያና ምላሽ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

## ፲፩. የእጣ ድልድል አዘገጃጀትና ትግበራ

፩. በኤጀንሲው የቴክኒክ ኮሚቴ ማጣራት ተደርጎ መስፈርቱን ያሟሉና የተመረጡ የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅቶች የስራ ቦታ ድልድል ሁሉም ተወዳዳሪዎች በተገኙበት በእጣ በህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበሩ ስም የሚደለደል ይሆናል፡፡ ይህ ማለት ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ እንዲያጓጉዝ

የሚመደበው ሙሉ ክፍለ ከተማውን ሳይሆን የተወሰኑ በህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

፪. የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅቶች የእጣ አወጣጥ የሚከናዎነው በድርጅቶች ስም ይሆናል፡፡ ይህ ማለት እጣው ሲጠቀለል ተሽከርካሪዎቹ ሳይሆን እጣ ውስጥ የሚገቡት የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅቱ ስም ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት ለምሳሌ ሁለት ተሽከርካሪ ያለው አንድ ድርጅት ሁለቱም ተሽከርካሪዎቹ የሚመደቡት ተመሳሳይ ቦታ ይሆናል፡፡

፫. መስፈርቱን አሟልቶ ለእጣ ድልድል የቀረበ ድርጅት አራትና በላይ ተሽከርካሪ ካለው እንደ ተሽከርካሪው መጠን የህብረት ሽርክና ማህበሩ የመሰብሰብ አቅሙ ተጠንቶ ድርጅቱ ሁለትና በላይ እጣ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ሁለትና በላይ ቦታዎች ላይ ገብቶ እንዲሰራ ሊደረግ ይችላል፡፡

፬. ከፍተኛ ቆሻሻ የሚሰበስቡ የህብረት ሽርክና ማህበራት ላይ ከቆሻሻው አቅም ጋር የሚመጣጠን ከአንድ በላይ የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት በጋራ እንዲሰሩ በእጣ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፭. የኤጀንሲው የደረቅ ቆሻሻ ማስተባበሪያ አገልግሎቶች ዳይሬክቶሬት በየአመቱ ለሚደረግ የእጣ ድልድል የህብረት የሽርክና ጽዳት ማህበራትን ቁጥርና የሚሰበስቡትን የቆሻሻ መጠን መሰረት ያደረገ ምድብ በማዘጋጀት ለማናጅምንት በማፀደቅ ለቴክኒካል ኮሚቴው እጣ እንዲያወጣበት ይደረጋል፡፡

፮. የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ቁጥር ካነሰና የህብረት ሽርክና ማህበሩ ቁጥር ከበዛ ተመሳሳይና ተቀራራቢ የሆኑ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራትን አንድ ላይ በማድረግ በአንድ አጓጓዥ ድርጅት እንዲጓጓዝላቸው ማድረግ ይቻላል፡፡ ነገር ግን የእጣ ቡድን ሲዘጋጅ ክፍለ ከተሞች ከተመደቡበት ምድብ ውጭ የህብረት የጽዳት ሽርክና ማህበርን ቡድን ማድረግ አይቻልም፡፡ ይህም ማለት በምድብ አንድ በሚገኘው ክፍለ ከተማ ውስጥ (ኮልፌ፤ ንፋስ ስልክ፤ አራዳ፤ ቂርቆስ፤ አዲስ ከተማና ልደታ) ሲሆን እነዚህ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኙ የህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበርን ከምድብ ሁለት (ቦሌ፤ የካ፤ አቃቂና ጉለሌ) ከሚገኙ የህብረት የጽዳት ሽርክና ማህበር ጋር አንድ ቡድን በማድረግና ለአንድ

አጓጓዥ እጣ ማዘጋጀት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም የማጓጓዣ ክፍያቸው የተለያየ በመሆኑ፡፡

፯. የራሳቸው ኮምፓክተር ኖሯቸው የራሳቸውን ደረቅ ቆሻሻ ብቻ የሚያጓጉዙ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት በእጣ ድልድል ውስጥ ሳይገቡ ቅድሚያ ለማህበሩ ይሰጣል፡፡ ነገር ግን እንደማንኛውም አጓጓዥ ድርጅት በምዝገባ ፕሮግራሙ መሰረት አስፈላጊውን መረጃ አሟልተው መመዝገብ ግዴታ አለባቸው፡፡

፰. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት እጣ ከወጣላቸው በኋላ ከኤጀንሲው ጋር ውል ከመዋዋሉ በፊት በግላቸው ከሚፈልገው ድርጅት ጋር በመነጋገር የተመደቡበትን የህብረት የሽርክና የጽዳት ማህበር መቀያየር ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ውል ከገባና ስራ ከጀመሩ በኃላ መቀያየር አይችሉም፡፡

፱. ተራ ቁጥር ፰ እንደተጠበቀ ሆኖ በግላቸው የተመደቡበትን የተቀያየሩ ድርጅቶች ተስማምተው መቀያየራቸውን የሚገልጽ የሁለቱም ድርጅቶች ማህተም ያረፈበት ሰነድ በደብዳቤ ለኤጀንሲው ማቅረብና ተቀባይነት ማግኘት ይገባዋል፡፡

## ፲፪. ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት የስራ ክልል

፩. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ስራውን የሚሰራው በህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ከቤት ለቤትና ከዞን ጽዳት የተሰበሰብን፣ በመንገድ ጽዳት፣ በህብረተሰብ የጽዳት ተሳትፎና በምግብ ዋስትና በተደራጁ አካላት የፀዳና የተሰበሰበን ደረቅ ቆሻሻ ኤጀንሲው በሚወስነው የማስወገጃ ቦታ፣ ማቃጠያ ወይም መልሶ መጠቀም ማዕከላት ድረስ የማጓጓዝ ግዴታ አለበት፡፡

፪. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ቆሻሻን ማጓጓዝ ያለበት ተወዳደርሮ ባሸነፈበትና በተመደበበት የህብረት የሽርክና ጽዳት ማህበራት ብቻ ነው፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፪ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ደረቅ ቆሻሻ በሚያጓጉዝበት ክፍለ ከተማ ውስጥ በተለያዩ ምክንያት የተከማቸ ቆሻሻ ካለ ክፍለ ከተማው በደብዳቤ ለአጓጓዥ ድርጅቱ እዲያጓጉዝለት ከጠየቀው በጊዚያዊነት አንድ ወር

ላልሞላ ጊዜ ከስራ ቦታው ውጪ በሌላ ቦታ ገብቶ የሌላ የሸርክና ማህበርን ደረቅ ቆሻሻ ወይንም በዘመቻ የተፀዳ ቆሻሻን ሊያጓጉዝ ችላል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፫ በተገለፀው መሰረት በተለያዩ ምክንያት ከተመደበበት ሽርክና ጽዳት ማህበር ውጪ በልዩ ድጋፍ በጊዚያዊነት ሌላ ቦታ ላይ ደረቅ ቆሻሻ እዲያጓጉዝ በክፍለ ከተማው የተመደበ የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት በዋናነት በቋሚነት የተመደበበት የህብረት ሽርክና ማህበር በውሉ መሰረት የማገልገል ግዴታ አለበት፡፡

## ፲፫. የህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበራት ደረቅ ቆሻሻን ለማጓጓዝ የፈቃድ አሰጣጥ

፩. ማንኛውም የህብረት የሽርክና የጽዳት ማህበር በራሱ የስራ ክልል ውስጥ የሰበሰበውን ደረቅ ቆሻሻ እስከ ማስወገጃ ቦታ ማጓጓዝ ከፈለገ በአንቀጽ ፺ ቁጥር ፩ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ማሟለት የሚገባው ሲሆን ነገር ግን የህብረት የሽርክና የጽዳት ማህበሩን ለመደገፍና ለማበረታታት ሲባል በዚህ መመሪያ በአንቀጽ ፺ ቁጥር ፩ ከተዘረዘሩት መካከል ቢያንስ ሁለት ኮምፓክተር ተሽከርካሪ የሚለው ተሻሽሎላቸው ቢያንስ አንድ ባለ 40 ሜትር ኩብ ኮምፓክተር የስራት ዘመኑ 20 ዓመት ያልበለጠው በህብረት የሽርክና የጽዳት ማህበሩ ስም ካላቸው ወደ ማጓጓዝ ስራው መግባት ይችላሉ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፩ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ተሽከርካሪ ብቻ ስራ የጀመረ የህብረት የሽርክና የጽዳት ማህበር በዓመቱ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ ፺ ቁጥር ፩ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ የማሟላት ግዴታ አለበት፡፡ ይህም ማለት በዚህ መመሪ በአንቀጽ ፺ ቁጥር ፩ የተዘረዘሩ ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው የተሽከርካሪውን ቁጥር ቢያንስ ወደ ሁለት የማሳደግ ግዴታ አለበት ይህን ካላሟላ ደረቅ ቆሻሻን የማጓጓዝ ውሉ በዓመቱ አይታደስለትም፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፩ የተዘረዘረው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት እራሱ የሰበሰበውን ደረቅ ቆሻሻ የአሰራር መመሪያውን አሟልቶ ማጓጓዝ ከፈለገ ያለውድድር የማጓጓዝ ፈቃድ

እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡ ነገር ግን የማጓጓዣ ክፍያ ዋጋው የሸርክና ማህበሩ በሚሰራበት ክፍለ ከተማ የምድብ ዋጋ ተመን መሰረት ብቻ ይሆናል፡፡

፬. ማንኛውም የህብረት የሸርክና የጽዳት ማህበር ከራሱ ማህበር ውጭ የሌሎችን የህብረት የሸርክና የጽዳት ማህበር ደረቅ ቆሻሻን እስከ ማስወገጃ ቦታ ማጓጓዝ ከፈለገ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ ፺ ቁጥር ፩ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ሙሉ በሙሉ አሟልቶ እንደማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት በውድድር ብቻ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

፭. ማንኛውም በደረቅ ቆሻሻን አጓጓዥ ድርጅት የተሰማራ የህብረት የሸርክና የጽዳት ማህበር ለሚያጠፏቸው ጥፋቶች እንደ ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት እኩል ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡ ይህ ማለት በማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት የተጣሉ የዚህ መመሪያ አንቀጽ ግዴታዎች በሙሉ በህብረት የሸርክና የጽዳት ማህበር ተደራጅተው ደረቅ ቆሻሻ በሚያጓጉዙ ሸርክናዎች ላይም ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፮. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻን እሰከ ማስወገጃ ቦታ የሚያጓጉዝ የህብረት የሸርክና የጽዳት ማህበር እንደማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ እንደሚያጓጉዝ ድርጅት ከኤጀንሲና ከክፍለ ከተማ ጋር የስራ ውል የመግባት ግዴታ አለበት፡፡

፯. ማንኛውም የህበረት የሸርክና የጽዳት ማህበር የሰበሰበውን ደረቅ ቆሻሻ ሌላ የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ድርጅት እንዲያጓጉዝ ፈቃድ ከተሰጠውና ውል ከገባ በኋላ የህብረት የሸርክና ጽዳት ማህበሩ ተሸከርካሪ ቢገዛና ስራ የጀመረው አጓጓዥ ድርጅቱ ውሉ ሳይጠናቀቅ ማህበሩ ተሸከርካሪ ስለገዛሁ ደረቅ ቆሻሻውን እኔው አጓጉዛለሁ ቢል ስራ የጀመረው ድርጅት ውሉ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ለህብረት የሸርክና የጽዳት ማህበሩ የማጓጓዝ ፈቃድ አይሰጠውም፡፡

## ፲፬. የውል ስምምነት መፈራረም

፩. በመስፈርቱ አሟልቶ የተመርጠ ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዝ ድርጅት አገልግሎት ለመስጠትና ለሚሰራው ስራ ህጋዊ ክፍያ ለመጠየቅ እንዲያስችለው ከደረቅ ቆሻሻ አስተዳዳር ኤጀንሲ ጋር የውል ስምምነት መፈራረም ይገባዋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፩ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ከኤጀንሲው ጋር ውል ተፈራርሞ የስራ ፈቃድ ደብዳቤ ከተሰጠው በኋላ ስራውን ከሚሰራበት የክፍለ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ጋር የስራ ውል ይፈራረማል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፪ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ከክፍለ ከተማ ጋር የሚደረግ ውል ከእያንዳንዱ የህብረት የሸርክና የጽዳት ማህበር ደረቅ ቆሻሻ የሚያነሳበትን በሰዓት የተገለፀ ፕሮግራምና የሸርክና ማህበራትና የድርጅቱን መብት፣ ግዴታና የተጠያቂነት ሁኔታ በግልጽ ያካተተ መሆን ይገባዋል፡፡

፬. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ ለማጓጓዝ የተመረጠ ድርጅት የስራ የውል ስምምነት ግዴታ የሚገባውና የሚፈራረመው ለአንድ ዓመት ብቻ ነው፡፡

፭. በዚህም መሰረት የአንድ አመቱ ውል ሲጠናቀቅ ኤጀንሲው አዲስ ማስታወቂያ በማውጣትና አዲስ ምዝገባ በማካሄድ በዚህ መመሪያ መሰረት አዲስ ድልድል ያከናዎናል፡፡

፮. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፭ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በኤጀንሲው አሳማኝ ችግር ምክንያት የአንድ ዓመት የውል ዘመኑ ተጠናቆ በአዲስ መልክ ድልድል ካልተደረገ ችግሩን ለኤጀንሲው ማናጅመንት አቅርቦ በማፀደቅ ለሶስት ወር ብቻ ውሉ እንዲራዘም በማድረግ በዚህ መመሪያው መሰረት አዲስ ድልድል ይደረጋል፡፡

፯. ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዝ ምደባ የተሰጠው ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት በስራ ላይ ችግር ከፈጠረ፣ በማንኛውም ሁኔታ መስራት በማይችልበት ደረጃ ከደረሰና ከመመሪያውና ከውል ውጪ ስራዎችን ሲሰራ ከተገኘ በማንኛውም ሰዓት ኤጀንሲው ውሉን አቋርጦ በመመሪያው መሰረት አዲስ ድልድል እስከሚደረግ ድረስ ኤጀንሲው በማናጅምንት አስወስኖ የተሻለ አፈጻጸም ያለውን ድርጅት በጊዚያዊነት ማሰራት ይችላል፡፡

## ፲፭. ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አጓጓዝ

፩. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ ሲያጓጉዝ ኤጀንሲው በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት ብቻ መከናዎን ይገባዋል፡፡

፪. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ወደ ማስወገጃ ቦታ ወይም ወደ ማቃጠያ ማዕከል እንዳይገቡ የተከለከሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን ማጓጓዝ የተከለከለ ነው፡፡

፫. የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ ካስቀመጠው የማስወገጃ፣ የማቃጠያ ወይም የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከል ውጭ ደረቅ ቆሻሻን ማስወገድ የተከለከለ ነው፡፡

፬. ከኤጀንሲ የስራ ፈቃድ የሌለው ማንኛውም አካል ደረቅ ቆሻሻን ማጓጓዝ የተከለከለ ነው፡፡

## ፲፮. የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት የአገልግሎት ክፍያ ስርዓት

፩. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ ላጓጓዘበት ክፍያ የሚከፈለው ኤጀንሲው በአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ አፀድቆ በሁለት ምድብ ከፍሎ ባስቀመጠው የቁርጥ ዋጋ ተመን መሰረት ብቻ ነው፡፡

፪. ለደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ ላጓጓዘበት ክፍያ ኤጀንሲው በውሉ መሰረት በሜትር ኩብ ወይም በኪሎ ግራም አስልቶ የሚከፍል ይሆናል፡፡ ነገር ግን በውሉ ላይ በኪሎ ግራምና በሜትር ኩብ ምን ያክል እንደሚከፈል በግልጽ መቀመጥ አለበት፡፡

፫. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ ላጓጓዘት ክፍያ በወሩ መጨረሻ የክፍለ ከተማው ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ያረጋገጠበት የክፍያ ሰነድ ሲቀርብ በኤጀንሲው ተከፋይ ይሆናል፡፡

፬. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ስራውን ለመስራት ውል ሲገባ ከተቀመጠው የክፍያ ዋጋ ውጭ ስራውን ከጀመረ በኋላ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ማቅረብም ይሁን ስራውን ማቋረጥ አይቻልም፡፡

፭. ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዝ ድርጅት ለስራው አስፈላጊ የሆነውን ማንኛውንም ወጭ (ለምሳሌ የሰራተኛ ደሞዝ፣ የተሽከርካሪ ነዳጅና ዘይት፣ የጥገና፣

የሰራተኛ ጥቅማጥቅም፣ የኢንሹራንስ፣ የተለያዩ ቅጣቶች፣ የማስወገጃ ቦታ ክፍያ፣ ፓርኪንግ ወዘተ) በሙሉ በራሱ የሚሸፍን ሲሆን ኤጀንሲው ለማጓጓዝ አገልግሎቱ ብቻ በውሉ ላይ በቀረበው ዋጋ መሰረት ይከፍላል፡፡

፯. ኤጀንሲው ክፍለ ከተማው እያረጋገጠ ለክፍያ የሚልከውን መረጃ በመስክ ወደ ክፍለ ከተማው በመውረድ የመረጃዎች ትክክለኛነትን ያረጋግጣል፡፡

## ፲፯. ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት የተሽከርካሪ ዓይነት

፩. በከተማችን ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዝ ድርጅት የተሽከርካሪ ዓይነት ኮምፓክተር ብቻ መሆን ይገባዋል፡፡

፪. ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዝ ድርጅት ተሽከርካሪ የመጫን አቅም 40 ሜትር ኩብ እና በላይ መሆን ይገባዋል፡፡

፫. ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዝ ድርጅት የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 2 መሆን ይገባዋል፡፡ ነገር ግን አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ያለው ድርጅት ከሆነ የዚህን መመሪያ መስፈርት ከሚያሟላ ሌላ አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ካለው ድርጅት ጋር በግሉ ተቀናጅቶ መስራት ይችላል፡፡

፬. ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዝ ድርጅት ተሽከርካሪው ላይ የድርጅቱ ስም በሁለቱም ጎን ጽፎ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

፭. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ ለማጓጓዝ የሚሰማራ ድርጅት ወይንም ማህበር ተሽከርካሪ ከመግዛቱ በፊት በቅድሚያ ኤጀንሲውን በደብዳቤ መጠየቅና ለመግዛት የድጋፍ ደብዳቤ ከኤጀንሲው ማግኘት አለበት፡፡ ነገር ግን ከኤጀንሲው እውቅና ውጪ በግላቸው ተሽከርካሪ ገዝተው ኤጀንሲው ወደ ስራ እንዲያስገባላቸው የሚጠይቁ የህብረት ሽርክና ማህበራትም ይሁን የግል ድርጅት ኤጀንሲው አያስተናግድም፡፡

፮. በስራ ላይ የሚገኝ ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ወይም ማህበር ስራ ከጀመረ በኋላ ከኤጀንሲው እውቅና ውጪ ተጨማሪ ተሽከርካሪ ገዝቶ ወደ ስራ ማስገባት ወይም እንዲገባለት መጠየቅ አይችልም፡፡

## ፲፰. የደህንነት መጠበቂያና ግብዓት ስለማሟላት

፩. ማንኛው ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ደረቅ ቆሻሻን ሲያጓጉዝ ቀይ አንጸባራቂ ልብስ፣ ማስክ፣ ሄልሜት፣ የደህንነት ጫማና ባጅ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፪. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ሹፌርና ረዳት ሰማያዊ ሙሉ ቱታ (ሸሚዝና ሱሪ) የመልበስ ግዴታ አለባቸው፡፡

፫. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዝ ድርጅት የሰራተኞቹ ቱታ ሁሌም ንፁህ እንዲሆን የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ ይህንን ያላሟላ ድርጅት ወደ ማስወገጃ ቦታ ገብቶ ቆሻሻውን መድፋት አይችልም፡፡

## ፲፱. የስራ አገልግሎት ውል ስለመሰረዝ

፩. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዝ ድርጅት  የአካባቢ ጥበቃ ህጎችን ከተላለፈ፣ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ህግ፣ ደንብ ከተላለፈ፣ የማጭበርበር ተግባር ሲፈጽም ከተገኘ፣ ከተመደበበት ክልል ውጭ ደረቅ ቆሻሻ ሲሰበስብና ሲያጓጉዝ ከተገኘ የገባው ውል ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተሰርዞ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፪. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት አገልግሎቱን ከሚሰጣቸው የህብረት የሽርክና የጽዳት ማህበራት ጋር ተደጋጋሚ ቅሬታ ካስከተለና በመረጃ ኤጀንሲው ካረጋገጠ፣ በውሉ መሰረት ስራውን ማከናዎን ካልቻለ፣ በማስወገጃ ቦታ እንዳይገቡ የተከለከሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን ይዞ ከገባ፣ ለስራው በቂ ተሽከርካሪ ካላቀረበ፣ ደረቅ ቆሻሻን ለማንሳት ባስቀመጠው ሰዓት መሰረት ካላነሳ፣ ለሁለት ጊዜ በኤጀንሲው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ተደርጎ ከጥፋቱ ካልታረመ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውሉ ተሰርዞ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፫. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በውሉ በተቀመጠው ቀንና ሰዓት መሰረት ደረቅ ቆሻሻውን ካልጫነ ወይንም የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት በውሉ በተቀመጠው ቀንና ሰዓት  መሰረት ደረቅ ቆሻሻውን ካልጫነ በዚህ ምክንያት ለሚደርስ ኪሳራ ችግሩን የፈጠረው አካል ኪሳራውን እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## ፰. ተቀናጅተው ስለሚሰሩ የደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅቶች ግዴታ

፩. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ያለው ከሆነ ከሌላ አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ካለው ድርጅት ጋር በግሉ ተቀናጅቶ መስራት ይችላል፡፡ ይህ ማለት በአንድ ድርጅት ስም ተጠቃለው ይሰራሉ ማለት ሳይሆን በጋራ እንደ አንድ ሆነው ለመስራት እርስ በእርሳቸው በህጋዊ ማስረጃ ተፈራርመው የተፈራረሙበትን የውል ሰነድ ያቀርባሉ ማለት ነው፡፡

፪. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ያለው ከሆነ ከሌላ አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ካለው ድርጅት ጋር በግሉ ተቀናጅቶ የሚሰራ ከሆነ ከኤጀንሲ ጋር የሚገባው ውል እስከሚጠናቀቅ ድረስ በጋራ የመስራት ግዴታ አለባቸው፡፡ ይህም ድርጅቶቹ እርስ በእርስ በሚዋዋሉት ውል ላይ ይካተታል፡፡

፫. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ያለው ሆኖ ከሌላ አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ካለው ድርጅት ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራ ከሆነ ማንኛውም የአገልግሎት ክፍያ የሚከፈላቸው በየግል ድርጅታቸው ስም ይሆናል፡፡ ነገር ግን ሁለቱ ድርጅቶች ሚዋዋሉት ውህደት በጋራ ለመስራትና አንዱ ተሽከርካሪ ቢበላሽ በሌላኛው ተሽከርካር እንዲጓጓዝ ለማድረግ ነው፡፡

፬. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት በቅንጅት ከሌላ ድርጅት ጋር ሆኖ እየሰራ ቢሆንና አንደኛው ድርጅት በቅጣት ወይንም በተለያዩ ምክንያቶች ውል ቢያቋርጥ በስራ ላይ የቀረው ድርጅትም ውሉ እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን በሌላኛው ጥፋት ምክንያት ውሉ የተቋረጠበት ድርጅት ከሌላ ድርጅት ጋር ተቀናጅቶ ወደ ስራ እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

፭. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት በቅንጅት ከሌላ ድርጅት ጋር ለመስራት ተስማምተው ምዝገባ ካደረጉ በኋላ አንደኛው ድርጅት የቴክኒካል ምዘናውንውን አልፎ ሌላኛው ደግሞ ካላለፈ ሁለቱም ድርጅቶች እዳይወዳደሩ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን ቴክኒካል ኮሚቴው ችግሩን በማናጅምንት አስወስኖ አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ኖሯቸው የቴክኒካል ምዘናውን የሚያሟሉ አጓጓዥ ድርጅቶችን ስማቸውን በማስታወቂያ ቦታ በመለጠፍ በራሳቸው ተነጋግረው

እንደገና በአጭር ቀን ውስጥ በውል ተፈራርመው በእጣው እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡

## ፳፩. የግል የጽዳት ድርጅቶች በደረቅ ቆሻሻ አጓጓዝ የሚደረግ ምዝገባ

፩. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት በደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዝ ለመሳተፍ ከፈለገ በቅድሚያ ለመመዝገብ የሚያስችለው የድግፍ ደብዳቤ ከኤጀንሲው ሊኖረው ይገባል፡፡

፪. ኤጀንሲው ለማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት በደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዝ ስራ እንዲሳተፉ የሚሰጠው የድጋፍ ደብዳቤ የግል የጽዳት ድርጅቱ አሁን ተመድቦ በሚሰራበት ቦታ ላይ በቂ ተቋማትና ቆሻሻ እያገኘ አለመሆኑን በየወሩ ከሚከፈል ክፍያ ሰነድ ላይ የሚያገኘው ገቢ አጠቃላይ መነሻ በማድረግ ወይንም እያጓጓዘ ያለው ቆሻሻ መጠን ዝቅተኛ መሆኑን ሲያረጋግጥ ብቻ ነው፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፪ በተገለፀው መሰረት ወደ ደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዝ እንዲወዳደሩ ኤጀንሲው ድጋፍ የሰጣቸው የግል ጽዳት ድርጅቶች ኤጀንሲው በሚወስነው ውሳኔ መሰረት ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል ከሚሰሩበት የተቋማት ደረቅ ቆሻሻ ማሰባሰብና ማጓጓዝ ስራ እንዲለቁ ሊደረግ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

**የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት**

### ፳፪. የኤጀንሲው ተግባርና ኃላፊነት

፩. ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅቶችን በየዓመቱ እያወዳደረ ድልድል ይሰጣል፡፡

፪. የግል የጽዳት ድርጅቶች በደረቅ ቆሻሻ አጓጓዝ ዘርፍ ለመወዳደር ጠያቄ ሲያቀርቡ በመመሪያው መሰረት እዲስተናገዱ ያደርጋል፡፡

፫. የደረቅ ቆሻሻን አጓጓዥ ድርጅት ክፍያን ከክፍለ ከተማ የቀረበ የክፍያ ማስረጃን አጣርቶ ክፍያ ይፈጽማል፡፡

፬. በህጋዊ መንገድ ደረቅ ቆሻሻን ለማጓጓዝ ከተመረጠው ድርጅት ጋር የውል ስምምነት ይፈራረማል በውሉ መሰረትም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡ ችግር ሲፈጠርም የማስተካከያ እርምጃ በውሉ መሰረት ይወስዳል፡፡

፭. አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘና የወቅቱን የገበያ ሁኔታ ካስገደደ ኤጀንሲው የገበያ ጥናት በማድረግ በከተማ ካቢኔ እንዲፀድቅ የዋጋ ማሻሻያ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን ከውል በኋላ የሚደረግ የክፍያ ማስተካከያ አይኖርም፡፡

### ፳፫. የክፍለ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

፩. ኤጀንሲው ለይቶ በደብዳቤ ከላከው በክፍለ ከተማው ደረቅ ቆሻሻ ከሚያጓጉዘው ድርጅት ጋር የስራ ውል ይፈራረማል፡፡

፪. በክፍለ ከተማው ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዘው ድርጅት በውሉ መሰረት ስራውን መስራቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡፡

፫. ቆሻሻውን ከሚያጓጉዘው ድርጅትና ከህብረት የሽርክና የጽዳት ማህበራት ጋር ቋሚ ወርሃዊ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ያጋጥሙ ችግሮችን በጋራ ይፈታል፡፡

፬. በክፍለ ከተማው ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዘው ድርጅት እንቅስቃሴን በመገምገም በየወሩ ለኤጀንሲው ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፫. በየወሩ ደረቅ ቆሻሻ የአጓጓዥ ድርጅቱ ክፍያን በማጣራት ለኤጀንሲው የክፍያ ሰነድ ያቀርባል፡፡

፬. በውላቸው መሰረት የማይሰሩ ድርጅቶችን በማጣራት ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ይሰጣል፡፡ ነገር ግን ሊታረሙ ያልቻሉና ከፍተኛ ችግር ያለባቸው ከሆነ ውላቸው እንዲቋረጥ ለኤጀንሲው የውሳኔ ሀሳብ በደብዳቤ ያቀርባል፡፡

፭. ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዘው ድርጅት ውሉ ሲታደስ የድጋፍ ደብዳቤ አጣርቶ ለድርጅቱ ይጽፋል፡፡

## ፳፬. የወረዳ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

፩. የሸርክና ማህበራት በተፈቀደላቸው ጊዚያዊ ማከማቻ ቦታ ብቻ ደረቅ ቆሻሻ እንዲያስቀምጡ ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፡፡

፪. ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዘው ድርጅት በገባው ውል መሰረት ከህብረት የሸርክና የጽዳት ማህበራት፤ ከመንገድ ጽዳት፤ በህብረተሰብ የጽዳት ተሳትፎ፤ ከምግብ ዋሰትና ከተደራጁ የተሰበሰበ ደረቅ ቆሻሻ ማንሳቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡፡

፫. የሚከማቸው ደረቅ ቆሻሻ አካባቢን በማያቆሽሽ መልኩ መሆኑን ይከታተለል፤ ይቆጣጠራል፡፡

፬. ቆሻሻው በሚጫንበት ቦታ በመገኘት ተገቢነቱን እዲረጋግጥ ያደርጋል፡፡

፫ ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት በገባው ውል መሰረት ደረቅ ቆሻሻውን ማንሳቱን በመስክ በመውረድ ይከታተላል፡ይቆጣጠራል፡፡

## ፳፫. ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት ተግባርና ኃላፊነት

፩. ወደ ማስወገጃ ቦታ፤ ማቃጠያ ማዕከላት ወይም ለመልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከላት የሚጓጓዙ ደረቅ ቆሻሻዎች ኤጀንሲ ባወጣው ስታንዳርድ መሰረት ማከናዎን ይገባዋል፡፡

፪. ወደ ማስወገጃ ቦታ እንዳይገባ የተከለከለ ደረቅ ቆሻሻን ጭኖ በመሄድ በማስወገጃ ቦታ ላይ በድርጅቱና በኤጀንሲው ለሚደርስ ማንኛውም ኪሳራና ጉዳት ቆሻሻውን ያጓጓዘው ድርጅት ኃላፊነትን ይወስዳል፡፡

፫. በገባው ውል መሰረት በተመደበበት የህብረት ሽርክና ማህበር የተሰበሰበውን ደረቅ ቆሻሻ የማጓጓዝ ግዴታ አለበት፡፡

፬. ከተመደበበት ቦታ ውጭ ደረቅ ቆሻሻን ማጓጓዝ አይችልም፡፡

፭. የደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዝ ድርጅቶች የመኪና መበላሸት ወይም ችግር ቢገጥመው በአፋጣኝ ሌላ መኪና በመመደብ ለኤጀንሲውና ለክፍለ ከተማው የተቀየረውን ተሽከርካሪ ታርጋ በደብዳቤ በማሳወቅ አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፮. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዝ ድርጅት ከህብረት የሽርክና የጽዳት ማህበራት፤ ከአካባቢው ህብረተሰብ፤ ከማስወገጃ ቦታ ከሚሰሩ ሰራተኞች ጋር ተግባብቶ የመስራትና የሚጫነው ደረቅ ቆሻሻ ተገቢነቱን ሲጫን ቆሞ አረጋግጦ የመጫን ግዴታ አለበት፡፡

፯. ከህብረት የሽርክና የጽዳት ማህበራት ጋር መተማመን እንዲፈጥር ደረቅ ቆሻሻውን ሲያጓጉዝ (ሲያነሳ) የድርጅቱ ማህተም ያለበትን ደረሰኝ ወይም የሽርክና ማህበራት በሚያዘጋጁት ሰነድ ላይ ቆሻሻ ያነሳበትን ቀንና ሰዓት በሚገልጽ ሁኔታ የመፈረም ወይም ለማህበራቱ ሰብሳቢ (ተወካይ) የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፰. ከህብረት የሽርክና የጽዳት ማህበራት አጓጉዞ ለተወገደ ደረቅ ቆሻሻ ደረሰኙን በእለቱ ወይም ከክፍለ ከተማው ጋር በገባው ውል መሰረት የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡

፱. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ የሚያጓጉዝ ድርጅት ማስወገጃ ቦታ የሚያስቆርጠው ደረሰኝ በህብረት የሽርክና የጽዳት ማህበሩ ስም መሆን አለበት፡፡

፲. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ አጓጓዥ ድርጅት የህብረት ሽርክና ማህበራትን ደረሰኝ ቢጥል በተወገደው ቆሻሻ ልክ ክፍያውን ከግሉ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

## ፳፮. የሽርክና ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት

፩. ደረቅ ቆሻሻና ከመኖሪያ ቤት በስታንዳርዱ መሰረት በመሰብሰብ በተፈቀደላቸው የጊዜያዊ ማቆያ ቦታ ብቻ ማከማቸት፡፡

፪. ወደ ማስወገጃ ቦታ እንዳይጓጓዙ የተከለከሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን መለየትና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፡፡ ነገር ግን ሳይለዩ ወደ ማስወገጃ ቦታ ለሚጓጓዙ ደረቅ ቆሻሻዎች ለሚደርስ ማንኛውም ችግር ሙሉ ኃላፊነቱን የሽርክና ማህበሩ ይወስዳል፡፡

፫. የተሰበሰበሰው ደረቅ ቆሻሻ አካባቢን በማያቆሽሽ መልኩ በስታንዳርዱ መሰረት ማከማቸት አለበት፡፡

፬. ከድርጅቱ ጋር በገቡት ፕሮግራም መሰረት ደረቅ ቆሻሻውን ወደ ተሽከርካሪው የመጫን ግዴታ አለባቸው፡፡

፭. በገቡት ውል መሰረት የሚፈለገውን የቆሻሻ መጠን በየቀኑ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡ ለመቻን በተስማሙት ሰዓት መሰረት ቆሻሻውን የመቻን ግዴታ አለባቸው፡፡

፮. ማስወገጃ ቦታ የተቆረጠላቸውን ደረሰኝ በወቅቱ ከድርጅቱ አረጋግጠው በፊርማ መረከብ አለባቸው፡፡ ይህንን ሳያደርጉ ለሚከሰት ማንኛውም ችግር ኃላፊነቱ ለህብረት ሽርክና ማህበሩ ይሆናል፡፡

## ፳፮. የተጠያቂነት ስርዓት

- ማንኛውም አካል በዚህ መመሪያ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ካልፈፀመ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ፳፯. መመሪውያውን ስለማሻሻል

- ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በኤጀንሲው ሊሻሻል ይችላል

## ፳፰. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

- ይህ መመሪያ ከዛሬ 05/09/2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

# በአዲስ አባባ ከተማ አስተዳዳር
# የደረቅ ቆሻሻ አስተዳዳር ኤጀንሲ